**የኮሮና ቫይረስ በሽታን (COVID-19) ለመከላከል ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱትን ኮሚርንታሪ (COMIRNATY) (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ ፋይዘር ባዮቴክ (PFIZER-BIONTECH) የCOVID-19 ክትባትን፣ እና የፋይዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (BIVALENT) (ኦሪጅናልና ኦሚክሮን BA.4/BA.5) በተመለከተ ለክትባቶቹ ወሳጆችና ተንከባካቢዎች መረጃ ለመስጠት የቀረበ የክትባት መረጃ ቅጽ**

**ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ**

**በSARS-CoV-2 ምክንያት የሚመጣውን የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019ን (COVID-19) ለመከላከል ኮሚርንታሪ/ COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent (ኦሪጅናል እና ኦሚክሮን BA.4/BA.5)፣ ከዚህ በኋላ የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ተብሎ የሚጠራው ቀርበውልዎታል።**

**ይህ ለተቀባዮችና ተንከባካካዎች የቀረበ የመረጃ መስጫ ቅጽ የመረጃ ቅጽ ስለ የፋይዘር ባዮቴክ (PFIZER-BIONTECH) የCOVID-19 ክትባት እና የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent የተመለከተ የመረጃ መስጫ ቅጽ ከመያዙም በተጨማሪ እድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ 1 ለሆኑ ሰዎች ጥቅም ላይ እንዲውል በዩኤስ የምግብና መድሀኒት አስተዳደር (FDA) ፍቃድ ስለተሰጠው የኮሚርንታሪ/ COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣mRNA) የተመለከተ መረጃ ይይዛል[1].**

**በFDA የተፈቀደው የኮሚርናቲ (Comirnaty) (የCovid-19 ክትባት፣ mRNA) እና በአስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ (EUA) ስር እድሜያቸው 12 ዓመት እና እና ከዛ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የተፈቀዱት ሁለቱ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ቀመሮች በየራሳቸው የአጠቃቀም መመሪያ መሰረት ሲዘጋጁ በተቀያያሪነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።[2]**

**ኮሚርናቲ (Comirnaty) (Covid-19 Vaccine, mRNA) በFDA የተፈቀደ በፋይዘር ባዮቴክ (PFIZER-BIONTECH) የተዘጋጀ የCovid-19 ክትባት ነው። ክትባቱ ዕድሜያቸው 12 አመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች COVID-19ን ለመከላከል በ2 ተከታታይ ዶዝ እንዲሰጥ የተፈቀደ ክትባት ነው። ክትባቱ በተጨማሪም በEUA ስር የሚከተሉትን እንዲያቀርብ ተፈቅዷል፡**

- **ዕድሜያቸው 12 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ የሰውነታቸው የበሽታ መከላከል አቅም በተወሰነ ደረጃ የተዳከመ ሰዎች ሶስተኛ የመጀመሪያ ተከታታይ ዙር ክትባት ለመስጠት፤**

---

[1] የልጅዎ እድሜ 11 ዓመት ቢሆንም እንኳን ይህንን የክትባት የመረጃ መስጫ ቅጽ ማግኘት ይችላሉ። በመጀመሪያው የክትባት ዶዞች በሚወስዱበት የጊዜ መካከል እድሜያቸው ከ11 ዓመት ወደ 12 ዓመት የሚቀየር ልጆች ከሁለቱም ዶዞች የትኛውንም መውሰድ ይችላሉ፤ ማለትም፣ (1) ዕድሜያቸው ከ 5 እስከ 11 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደውን የፋይዘር ባዮቴክ የCOVID-19 (Pfizer-BioNTech) COVID-19 ክትባትን፤ ወይም (2) ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተፈቀደላቸውን የኮሚርንታሪ (COMIRNATY) ወይም የፋይዘር ባዮቴክ የCOVID-19 (Pfizer-BioNTech) COVID-19 ክትባትን።

[2] በየራሳቸው የአጠቃቀም መመሪያ መሰረት ሲዘጋጁ በFDA የተፈቀደው የኮሚርናቲ (COMIRNATY) (የCovid-19 ክትባት፣ mRNA) እና በEUA ስር እድሜያቸው 12 ዓመት እና እና ከዛ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የተፈቀደው የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ምንም አይነት የደህንነት ወይም የውጤታማነት ስጋቶችን ሳያሳዩ በተቀያያሪነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

**የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ለሚከተሉት እንዲሰጥ የFDAን EUA አግኝቷል፡**

- ***ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች በሁለት ዶዝ የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት፣ እና***
- ***ዕድሜያቸው 12 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ የሰውነታቸው የበሽታ መከላከል አቅም በተወሰነ ደረጃ የተዳከመ ሰዎች ሶስተኛ የመጀመሪያ ተከታታይ ዙር ክትባት ለመስጠት፤***

**የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ለሚከተሉት እንዲሰጥ የFDAን EUA አግኝቷል፡**

- ***ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የየትኛውንም የተፈቀደ ወይም ፍቃድ የተሰጠው የCOVID-19 ክትባት የመጀመሪያውን ክትባት ወስደው ካጠናቀቁ ቢያንስ ከ2 ወራት በኋላ እንደ አንድ ኢጎዥ ዶዝ እንዲሰጥ፣ ወይም***
- ***ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የየትኛውንም የተፈቀደ ወይም ፍቃድ የተሰጠው የሞኖቫለንት[3] የCOVID-19 ክትባት በጣም የቅርብ ኢጎዥ ዶዝ ከወሰዱ ቢያንስ ከ2 ወራት በኋላ እንደ አንድ ኢጎዥ ዶዝ እንዲሰጥ።***

---

ይህ የክትባት የመረጃ ቅጽ በአሁኑ ወቅት የCOVID-19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ምክንያት ሊወስዱት ስለሚችሉት ስለ የኮሚርናቲ (COMIRNATY) (የCovid-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ክትባት ስጋቶችና ጥቅሞችን ለመረዳት የሚረዳዎ መረጃ ይዟል። ጥያቄዎች ካሉዎ የክትባት አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

ይህ የመረጃ ቅጽ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል። በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጽ ለማግኘት እባክዎ www.cvdvaccine.comን ይመልከቱ።

**ከእነዚህ ክትባቶች ማናቸውንም ከማግኘትዎ በፊት ማወቅ ያለብዎት ኮቪድ-19 ምንድነው?**
የCOVID-19 በሽታ SARS-CoV-2 ተብሎ በሚጠራ የኮሮና ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። በቫይረሱ ከተያዘ ከሌላ ሰው ጋር ንክኪ በማድረግዎ ምክንያት በCOVID-19 ሊያዙ ይችላሉ። በሽታው በዋናነት ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ሊያጠቃ የሚችል የመተንፈሻ አካል ህመም ነው። በCOVID-19 የተያዙ ሰዎች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ ህመም የሚደርሱ የተለያዩ ምልክቶች እንደታዩባቸው ሪፖርት ተደርጓል። ምልክቶቹ ለቫይረሱ ከመጋለጥ በኋላ ከ2 እስከ 14 ቀናት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ። ምልክቶቹ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለትን፣ ሳልን፣ የትንፋሽ ማጠርን፣ ድካምን፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመምን፣ አዲስ የሚፈጠር የጣዕም ወይም ሽታ አለመለየትን፣ የጉሮሮ መሰርሰርን፣ የአፍንጫ ፈሳሽ መብዛትን፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስን፣ ተቅማጥን ሊይዙ ይችላሉ።

---

[3] ሞኖቫለንት/Monovalent የትኛውንም የኦሪጂናል የSARS-CoV-2 ብቻ ስፓይክ ፕሮቲንን የሚይዝ ወይም የሚቀይርን የተፈቀደ ወይም ፍቃድ የተሰጠው የCOVID-19 ክትባትን ይገልጻል።

**ኮሚርንታሪ/ COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋይዘር ባዮቴክ/ PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ እና የፋይዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ BIVALENT የሚገናኙት እንዴት ነው?**

የኮሚርናቲ (Comirnaty) (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) እና የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት በየራሳቸው የአጠቃቀም መመሪያ መሰረት ሲዘጋጁ በተቀያያሪነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) የተዘጋጀው ከኮሚርንታሪ (COMIRNATY) እና የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ጋር በተመሳሳይ ዘዴ ነው፣ ነገር ግን በSARS-CoV-2 የኦሚክሮን (Omicron) ዝርያ ምክንያት የሚመጣውን የCOVID-19 በሽታን ለመከላከል የሚያገለግል የኦሚክሮን (Omicron) ንጥረ ነገር ይይዛል።

ስለ EUA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ የመረጃ ቅጽ መጨረሻ ላይ "**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

**እነዚህን ክትባቶች ከመውሰድዎ በፊት ለክትባት አቅራቢዎ መግለጽ ያለብዎ ምንድን ነው?**
**ለክትባት አቅራቢዎ የሚከተሉትን ጨምሮ ስለ ሁሉም የጤና ሁኔታዎችዎ ይንገሩት:**

- የትኛውም አላርጂዎች ካሉብዎ
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) ያለብዎ ስለመሆኑ
- ትኩሳት ካለብዎ
- የደም መፍሰስ ችግር ወይም የደም መቅጠን ካለብዎ
- የበሽታ መከላከል አቅምዎ የተዳከመ ከሆነ ወይም የበሽታ መከላከል ስርአትዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መድሀኒት እየወሰዱ ከሆኑ
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የማርገዝ እቅድ ካሉዎ
- የሚያጠቡ ከሆነ
- ሌላ የCOVID-19 ክትባት ከወሰዱ
- ከክትባት ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው የነበር ከሆነ

**እነዚህ ክትባቶች የሚሰጡት እንዴት ነው?**

የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent፣ ወይም ኮሚርናቲ (Comirnaty) (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) በመርፌ መልኩ በጡንቻዎ ላይ ይሰጡዎታል።

የመጀመሪያ ክትባት: የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት እና ኮሚርንታሪ/ COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) በመጀመሪያ ተከታታይ ዶዞች ይሰጣሉ። ክትባቱ በ3 ሳምንታት ልዩነትበ2 ተከታታይ ዶዝ ይሰጡዎታል። የተወሰኑ አይነት የበሽታ መከላከል አቅም ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች ሁለተኛውን ዶዝ ከወሰዱ ቢያንስ ከ4 ሳምንታት በኋላ ሶስተኛው የመጀመሪያ ዶዝ ክትባት ሊሰጣቸው ይችላል።

አጋዥ ዶዝ: የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent የሚከተለው ከተወሰደ ቢያንስ ከ2 ወራት በኋላ እንደ አንድ አጋዥ ዶዝ ይሰጣል:

- የየትኛውም የተፈቀደ ወይም ፍቃድ የተሰጠው የCOVID-19 ክትባት የመጀመሪያው ክትባት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ወይም
- የየትኛውም የተፈቀደ ወይም ፍቃድ የተሰጠው የሞኖቫለንት የCOVID-19 ክትባት በጣም የቅርብ አጋዥ ዶዝ ከተወሰደ በኋላ

ክትባቱ ሁሉንም ሰው ላይከላከል ይችላል።

**ኮሚርንታሪ/COMIRNATYን (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋይዘር ባዮቴክ/ PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባትን፣ ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/ PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/BIVALENTን መውሰድ <u>የሌለበት</u> ማን ነው?**

በሚከተሉት ሁኔታዎች የትኛውንም እነዚህን ክትባቶች መውሰድ የለብዎትም:

- ቀደም ሲል የወሰዱትን የኮሚርንታሪ/ COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣mRNA) ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/ Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ከባድ የአለርጂ አፀፋዊ ምላሽ ካጋጠምዎት፣
- በእነዚህ ክትባቶች በየትኛውም ግብአት ምክንያት ከባድ አለርጂ አጋጥሞ ከነበረ።

**የእነዚህ ክትባቶች ግብዓቶች ምንድን ናቸው?**

ኮሚርንታሪ/COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA), የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት እና የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent የሚከተሉትን ግብዓቶች ይይዛሉ:

- mRNA፣ ሊፒዶች ((4-ሀይድሮክሲቡቲል)አዛንዲል)bis(hexane-6,1-diyl)bis(2-hexyldecanoate)፣ 2 [(ፖሊትሊን ግሎኮል)-2000]-N,N-ዳይትሬድሲላሴታሚድ፣ 1,2-ዲስትሮይልl-sn-ግሊሴሮ-3- ፎስፎኮሊን እና ኮሌስትሮል)።

እድሜያቸው 12 ዓመት እና እና ከዛ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የተፈቀዱት የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባቶች ከሚከተሉት የግብአት ስብስቦች መካከል 1ዱን ይይዛሉ፤ እየተሰጠ ያለው ክትባት የትኛው እንደሆነ የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ፥

- ፖታሺየም ክሎራይድ፣ ሞኖቤዚክ ፖታሺየም ፎስፌት፣ ሶዲየም ክሎራይድ፣ ዲያቤዚክ ሶዲየም ፎስፌት ዲሀይድሬት እና ሱክሮስ

ወይም

- ትሮሜታሚን፣ ትሮሜታሚን ሃይድሮክሎራይድ እና ሱክሮስ

ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የሚሰጠው የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent የሚከተሉትን ተጨማሪ ግብዓቶች ይይዛል:

- ትሮሜታሚን፣ ትሮሜታሚን ሃይድሮክሎራይድ እና ሱክሮስ

ኮሚርናቲ (COMIRNATY) (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) ከሚከተሉት የግብአት ስብስቦች መካከል 1ዱን ይይዛል፤ እየተሰጠ ያለው ክትባት የትኛው እንደሆነ የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ፥

- ፖታሺየም ክሎራይድ፣ ሞኖቤዚክ ፖታሺየም ፎስፌት፣ ሶዲየም ክሎራይድ፣ ዲያቤዚክ ሶዲየም ፎስፌት ዲሀይድሬት እና ሱክሮስ

ወይም

- ትሮሜታሚን፣ ትሮሜታሚን ሃይድሮክሎራይድ እና ሱክሮስ

**እነዚህ ክትባቶች ከዚህ ቀደም ጥቅም ላይ ውለው ያውቃሉ?**

በክሊኒካል ሙከራዎች ደግሞ፣ ወደ 23,000 የሚጠጉ እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ቢያንስ 1 የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) ዶዝ ወስደዋል። ከታህሳስ 11, 2020 ዓ.ም ጀምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በEUA ስር ፋይዘር ባዮቴክ/ Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባትን ወስደዋል።

በህክምና ሙከራ ወቅት ወደ 300 የሚጠጉ ዕድሜያቸው ከ55 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች በተለየ የኦሚክሮን/ Omicron ንጥረ ነገር ይዘቱ ከፋይዘር ባዮቴክ/ Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent የሚለየውን የባይቫለንት ክትባት አንዱን ዶዝ ወስደዋል።

**እነዚህ ክትባቶች የሚያስገኟቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?**

ኮሚርንታሪ/COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) እና የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት COVID-19ን እንደሚከላከሉ ታይቷል። FDA በSARS-CoV-2 የኦሚክሮን/ Omicron ዝርያ ምክንያት

የሚመጣውን የCOVID-19 በሽታ በተሻለ ሁኔታ ለመከላከል የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ጥቅም ላይ እንዲውል ፈቅዷል።

የክትባቱ ከCOVID-19 መከላከል የቆይታ ጊዜ በአሁኑ ወቅት አልታወቀም።

**የእነዚህ ክትባቶች ስጋቶች ምንድን ናቸው?**
እነዚህ ክትባቶች ከባድ የአለርጂ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስከትሉ የሚችሉበት በጣም አነስተኛ ዕድል አለ። ከባድ አለርጂ በዋናነት የሚያጋጥመው አንድ ዶዝ ከተወሰደ በኋላ ካሉት ጥቂት ዲቃዎች ጀምሮ እስከ 1 ሰአት ያክል ነው። በዚህም ምክንያት የክትባት አቅራቢዎ የክትባቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ክትባቱን በወሰዱበት ቦታ እንዲቆዩ ሊጠይቅዎት ይችላል። የከባድ አለርጂ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡

- የመተንፈስ ችግር
- የፊት ወይም ጉሮሮ እብጠት
- የልብ ምት መፍጠን
- ከባድ የሙሉ ሰውነት መንደብደብ
- መደበትና ድካም

ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) በጥቂት ኮሚርንታሪ/COMIRNATY (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት በወሰዱ ሰዎች ላይ የተከሰተ ሲሆን፣ ይህም በአብዛኛው ከሴቶች እና እድሜያቸው ከገፋ ወንዶች ይልቅ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያሉ እና እድሜያቸው ከ 40 ዓመት በታች በሆኑ አዋቂ ወንዶች ላይ በይበልጥ ተስተውሏል። በእነዚህ አብዛኞቹ ሰዎች ላይ ምልክቶቹ መታየት የጀመሩት የክትባቱ ሁለተኛውን ዶዝ ከወሰዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ነው። ይህ የሚያጋጥምበት እድል በጣም ዝቅተኛ ነው። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የትኛውም የሚከተሉት ምልክቶች ከታዩብዎ ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ያድርጉ፡

- የደረት ህመም
- ትንፋሽ ማጠር
- የፈጣን አተነፋፈስ፣ የልብ መርገብገብ ወይም መውጋት ስሜት

በእነዚህ ክትባቶች ላይ ሪፖርት የተደረጉ የጎኒዮሽ ውጤቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፥

- ከባድ አለርጂ
- እንደ መንደብደብ፣ ማሳከክ፣ ሽፍታ ወይም የፊት እብጠት የመሳሰሉ ከባድ ያልሆኑ አለርጂዎች
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- ክትባቱ በተወጋበት ቦታ የሚፈጠር ህመም
- ድካም
- የራስ ምታት
- የጡንቻ ህመም
- ብርድ ብርድ ማለት
- የመገጣጠሚያ ህመም
- ትኩሳት
- ክትባቱ በተወጋበት ቦታ የሚፈጠር እብጠት
- ክትባቱ በተወጋበት ቦታ የሚፈጠር የሰውነት መቅላት
- ማቅለሽለሽ
- ጥሩ ያልሆነ ስሜት
- የብሽሽት እብጠት

- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- ተቅማጥ
- ማስመለስ
- የእጅ ህመም
- ከክትባቱ ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው ያውቁ ከሆነ
- መፍዘዝ

እነዚህ ሁሉም በአንድ ጊዜ የሚያጋጥሙ የእነዚህ ክትባት የጎኒዮሽ ውጤቶች ላይሆኑ ይችላሉ። ከባድና ያልተጠበቁ የጎኒዮሽ ውጤቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። እነዚህ ክትባቶች ሊያስከትሏቸው የሚችሏቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች አሁንም በመጠናት ናቸው።

**የጎኒዮሽ ውጤቶች ካጋጠሙኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**
ከባድ አለርጂ ካጋጠመዎት ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል ይሂዱ።

የሚረብሹዎት ወይም የማይሄዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሉዎት ለክትባት አቅራቢው ወይም ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ።

የክትባቱን የጎኒዮሽ ውጤቶች ለFDA/CDC የክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ ሲስተም (VAERS) ሪፖርት ያድርጉ። የVAERS የነጻ ጥሪ መስመር 1-800-822-7967 ነው ወይም በኦንላይን በ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html ሪፖርት ያድርጉ። እባክዎ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ በሳጥን #18 ስር በሚገኘው የመጀመሪያው መስመር ላይ እንደአስፈላጊነቱ የኮሚርናቲ (Comirnaty) (የCovid-19 ክትባት፣ mRNA)፣ "የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት EUA" ወይም "የፋይዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/BIVALENT EUA" የሚለውን ያካቱ።

ከዚህ በተጨማሪም የጎኒዮሽ ውጤቶችን ለPfizer Inc. ከዚህ በታች በተገለጸው የግንኙነት መረጃ ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ።

| ድረ ገጽ | የፋክስ ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| www.pfizersafetyreporting.com | 1-866-635-8337 | 1-800-438-1985 |

በv-safe የሚመዘገቡበት አማራጭም ሊሰጥዎ ይችላል። V-safe የCOVID-19 ክትባትን ከወሰዱ ሰዎች ስላጋጠሟቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች ለማረጋገጥ የጽሁፍ መልእክትና የድረገጽ ጥናቶችን የሚጠቀም የፍቃደኝነት ስማርት ስልክን መሰረት ያደረገ መሳሪያ ነው። V-safe ለCDC ስለ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝነት ለመቆጣጠር የሚረዱትን ጥያቄዎች ይጠይቅዎታል። V-safe በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የሁለተኛውን ዶዝ ማስታወሻ ይሰጣል እንዲሁም ተሳታፊዎች የCOVID-19 ክትባትን መውሰዳቸውን ተከትሎ ከባድ የጤና ተጽእኖ እንደተፈጠረባቸው ሪፖርት የሚያደርጉ ከሆነ የቀጥተኛ የCDC የስልክ ክትትል ያደርጋል። እንዴት እንደሚመዘገቡ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: www.cdc.gov/vsafeን ይጎብኙ።

**ኮሚርንታሪ/COMIRNATYን (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋይዘር ባዮቴክ/ PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባትን፣ ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/ PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/BIVALENT ክትባትን ላለመውሰድ ብወስን ምን ይሆናል?**
በ EUA ስር፣ ከእነዚህ ክትባቶች የቱንም መውሰድ ወይም አለመውሰድ የእርስዎ ምርጫ ነው። ከእነዚህ ክትባቶች የቱንም ላለመውሰድ ቢወስኑ መደበኛ የህክምና እንክብካቤ ላይ ለውጥ አይፈጥርም።

**በኮሚርናቲ (Comirnaty) (የCovid-19 ክትባት፣ mRNA) ክትባት፣ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/BIVALENT ምትክ የሚቀርቡ ሌሎች አማራጮች አሉ?**
ለመጀመሪያው ክትባት፣ COVID-19ን ለመከላከል ሌላኛው አማራጭ ስፓይክፋክስ/SPIKEVAX (COVID-19 Vaccine, mRNA) በFDA-የተፈቀደ የCOVID-19 ክትባት ነው። የSARS-CoV-2 ኦሚክሮን/ Omicron ንጥረ ነገርን የሚይዙ የባይቫለንት ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች COVID-19ን የሚከላከሉ ክትባቶች ሊቀርቡ ይችላሉ።

**ኮሚርንታሪ/ COMIRNATYን (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባትን፣ ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/BIVALENTን ከሌሎች ክትባቶች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ መውሰድ እችላለሁ?**
እስከ አሁን ድረስ የኮሚርናቲ (Comirnaty) (የCovid-19 ክትባት፣ mRNA) ክትባት፣ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን፣ የፋይዘር ባዮቴክ/PFIZER-BIONTECH የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/BIVALENT ሌሎች ክትባቶች ጋር አብሮ ስለመስጠት በተመለከተ ለFDA የቀረበ ዳታ የለም። ኮሚርንታሪ/COMIRNATYን (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA)፣ የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባትን፣ ወይም የፋይዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/Bivalentን ከሌሎች ክትባቶች ጋር አብረው ስለመውሰድ ካሰቡ በአማራጮችዎ ላይ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።

**የበሽታ መከላከል አቅሜ የተዳከመ ከሆነ ምን ይሆናል?**
የበሽታ መከላከል አቅምዎ የተዳከመ ከሆነ ሶስተኛውን ተከታታይ የፋይዘር ባዮቴክ/ Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት ወይም ኮሚርንታሪ/COMIRNATYን (የCOVID-19 ክትባት፣ mRNA) ዶዝ ሊወስዱ ይችላሉ። ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የክትባቱን ኢጋዥ ዶዝ ከፋዝዘር ባዮቴክ/Pfizer-BioNTech የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ጋር ሊወስዱ ይችላሉ። ክትባቶቹ የበሽታ መከላከል አቅማቸው ለተዳመ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከCOVID-19 ላይከላከሉ ስለሚችሉ፣ ስለሆነም COVID-19ን ለመከላከል እንዲረዳዎ አካላዊ ጥንቃቄዎችን መከተልዎን መቀጠል አለብዎ። ከእርስዎ ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ መከተብ አለባቸው።

**ነፍሰ ጡር ወይም የማጠባ ቢሆን ምን ይሆናል?**
ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የሚያጠቡ ከሆነ ስለ አማራጮችዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

**እነዚህ ክትባቶች በCOVID-19 ሊያስይዙኝ ይችላል?**
አይ። እነዚህ ክትባቶች SARS-CoV-2 የማይይዙ በመሆኑ COVID-19 ሊያስይዙዎት አይችሉም።

**የክትባት ካርድዎን ይያዙ**
የመጀመሪያውን የCOVID-19 ክትባትዎን ሲወስዱ የክትባት ካርድ ይሰጥዎታል። ተመልሰው በሚመጡበት ወቅት ካርዱን መያዝዎን አይርሱ።

**ተጨማሪ መረጃ**
ጥያቄዎች ካሉዎ ከዚህ በታች የተገለጸውን ድረገጽ ይጎብኙ ወይም ከታች በተገለጸው ስልክ ቁጥር ይደውሉ። በጣም

የቅርብ የመረጃ ቅጾችን ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች የቀረበውን የQR ኮድ ስካን ያድርጉ።

| አለም አቀፍ ድረገጽ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|
| www.cvdvaccine.com | 1-877-829-2619<br>(1-877-VAX-CO19) |

**ተጨማሪ መረጃ እንዴት አገኛለሁ?**

- የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ።
- CDCን በ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/index.html ይጎብኙ።
- FDAን በ https://www.fda.gov/emergency-preparedness-and-response/mcm-legal-regulatory-and-policy-framework/emergency-use-authorization ይጎብኙ።
- የአካባቢዎን ወይም የግዛትዎን የማህበረሰብ ጤና መምሪያ ያነጋግሩ።

**የክትባት መረጃዬ የት ይመዘገባል?**
ክትባት አቅራቢው የክትባት መረጃዎን በግዛት/አካባቢ የክትባት መረጃ ሲስተም (IIS) ወይም ሌላ የተመደበ ሲስተም ላይ ሊያካትት ይችላል። ስለ IISዎች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: https://www.cdc.gov/vaccines/programs/iis/about.htmlን ይጎብኙ።

**እነዚህን የCOVID-19 ክትባቶች ለማግኘት የመከተቢያ ክፍያ እከፍላለሁ?**
አይ። በአሁኑ ወቅት ክትባት አቅራቢው የክትባቱን ዶዝ ለመስጠት ሊያስከፍልዎ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ የሚወስዱት የCOVID-19 ክትባትን ብቻ ከሆነ ለክትባቱ መውሰጃ ክፍያ ወይም የትኛውም ሌላ ክፍያ ከኪስዎ አይከፍሉም። ሆኖም የክትባት አቅራቢዎች ለክትባቱ ወሳጆች የCOVID-19 ክትባት መስጫ ክፍያዎች ሽፋን ከሚሰጥ ፕሮግራም ወይም እቅድ (የግል የመድን ዋስትና፣ Medicare፣ Medicaid፣ የጤና ድጋፎችና አገልግሎቶች አስተዳደር [HRSA] የመድን ዋስትና የሌላቸው ተቀባዮች የCOVID-19 የመድን ዋስትና የሌላቸው ፕሮግራም) ተገቢውን መልሶ ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ።

**የሚጠረጠሩ የማጭበርበር ጉዳዮችን የት ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?**
የCDC የCOVID-19 ክትባት ፕሮግራም መስፈርቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ስለ የትኛውም ጥሰቶች የሚያውቁ ግለሰቦች እነዚህን ለዩኤስ የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ የዋና መርማሪ ጽ/ቤት 1-800-HHS-TIPS ወይም https://TIPS.HHS.GOV።

**የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም ምንድን ነው?**
የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም (CICP) እነዚህን ክትባቶች ጨምሮ በተወሰኑ መድሀኒቶች ወይም ክትባቶች የተነሳ ከባድ ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች የሚከፍሏቸው የህክምና እንክብካቤ ወጪዎች እና ሌሎች ልዩ ወጪዎች እንዲከፈሏቸው የሚያግዝ የፌደራል ፕሮግራም ነው። በጠቅላላው የካሳ ጥያቄው ክትባቱ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በአንድ (1) አመት ውስጥ ለCICP መቅረብ አለበት። ስለዚህ ፕሮግራም የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.hrsa.gov/cicp/ ን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-855-266-2427 ይደውሉ።

**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**
የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) እንደ የወቅቱ የCOVID-19 ወረርሽኝ የመሳሰሉ የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ወቅ ክትባቶችን ጨምሮየህክምና ምርቶች እንዲቀርቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያመቻች አሰራር ነው። EUA በCOVID-19 ወረርሽኝ ቆይታ ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ መድሀኒቶችን እና የባዮሎጂካል ምርቶችን ለመጠቀም አሳማኝ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ይህን በሚፈቅደው የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (HHS) መግለጫ ድጋፍ አግኝቷል። በአስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ የተሰጠው ምርት ከ FDA ፍቃድ ካገኘ ምርት ጋር በ FDA አንድ አይነት የግምገማ ሂደት አይደረግለትም።

FDA የተወሰኑ መስፈርቶች ሲሟሉ EUA ሊሰጥ የሚችል ሲሆን መስፈርቶቹ በቂ፣ የተፈቀዱ፣ ዝግጁ አማራጮች አለመገኘትን ይይዛሉ። በተጨማሪም የFDA ውሳኔ በሚቀርቡለት ምርቱ በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት ወቅት COVID-19ን ለመከላከል ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል እና የምርቱ የታወቁና ሊሰሩ የሚችሉ ጥቅሞችን እና ከምርቱ የታወቁና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች ይልቅ ጥቅሞቹ እንደሚያመዝኑ በሚያሳዩ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሰረታል። በCOVID-19 ወረርሽ ወቅት ምርቱ ጥቅም ላይ እንዲውል ለመፍቀድ እነዚህ ሁሉም መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።

ካልተቋረጠ ወይም ካልተሻረ በስተቀር (ይህ ከሆነ ግን፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ምርቱ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም)፣ የ ኮቪድ-19 የ EUA አስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ አሰፈላጊነት እስካለ ድረስ፣ የዚህን ምርት EUA ተግባራዊ እንደሆነ የሚቆይ ይሆናል።

BIONTECH
የተመረተው ለ፥
BioNTech Manufacturing GmbH
An der Goldgrube 12
55131 Mainz, Germany

Pfizer
አምራች፥
Pfizer Inc., New York, NY 10017

LAB-1451-23.1c

የተሻሻለበት ቀን: 8 ታህሳስ 2022

ይህ የመረጃ ቅጽ ለኤሌክትሮኒክ የሕክምና መረጃዎች/የክትባት የመረጃ ሲስተሞች ለክትባት ተቀባዩ የቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ ስካን ያድርጉ።

GDTI: 0886983000332